# 2025 በዝቃጭ ማሸጊያ (SLURRY SEAL) እንደገና አስፋልት በነባሩ ላይ ማንጠፍ ፕሮጀክት

## ተደጋግመው የሚነሱ ጥያቄዎች

### የእግረኛ መዳረሻ

**ጥያቄ፦ የዝቃጭ ማሸጊያው ማንጠፍ በሂደት ላይ እያለ እኔ መንገዴን እንዴት መጠቀም እችላለሁ?**

መልስ፦ እርስዎ ያሉበት መንገድ በተያያዘው ካርታ ላይ በቀይ ምልክት ተደርጎበት ከሆነ፣ ያሉበት መንገድ ከጠዋቱ ሰአታት ጀምሮ እስከ ረፋዱ ከሰአት በኋላ የዝቃጭ ማሸጊያ ሂደት በሚካሄድበት ቀን ይዘጋል እና ከተጠናቀቀ በኋላ ከአራት እስከ ስድስት ሰአታት ውስጥ ተዘግቶ መቆየት አለበት፣ በዚህ ጊዜ በመንገድ ላይ መኪና ማቆም እና መንዳት አይፈቀድም። ነዋሪዎች፣ የንግድ ሥራዎች፣ እና ጎብኝዎች መንገዱ እንደገና እስኪከፈት ድረስ በዝቃጭ ማሸጊያው አካባቢ በእግር ከመሄድ እንዲቆጠቡ የሚበረታታ ቢሆንም፣ የእግረኛ መንገዱ ለአስፈላጊው መዳረሻ በዚህ ጊዜ ክፍት ይሆናል።

**ጥያቄ፦ መንገዴ የእግረኛ መንገድ የለውም። የዝቃጭ ማሸጊያው ማልበስ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ እንዴት በእግር እመላለሳለሁ? በመንገዱ ጠርዝ ላይ መሄድ እችላለሁ?**

መልስ፦ ነዋሪዎች፣ የንግድ ሥራዎች እና ጎብኝዎች በአጠቃላይ መንገዱ እስኪከፈት ድረስ ዝቃጭ ማሸጊያ እየተሰራ ባለበት አካባቢ በእግር እንዳይሄዱ የሚበረታታ ቢሆንም፣ በመሰራት ላይ ባሉ ጎዳናዎች ላይ የእግረኛ መንገዶች የሌሉ ከሆነ የፕሮጀክቱ ሰራተኞች የእግረኛ መንገዶችን ይጠርጋሉ። ለማስታወስ ያህል፣ ተነጥፎ ያልደረቀው ድብልቅ/ ዝቃጭ ከአልባሳት፣ ከጫማዎች ወይም ከመዳፎች ላይ ለማስወገድ አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት እግረኞች እና የቤት እንስሶች መንገዱ ለትራፊክ እስኪከፈት ድረስ ከዝቃጭ ማሸጊያ እቃው እንዲርቁ መጠንቀቅ አለባቸው።

### የተሽከርካሪ መዳረሻ

**ጥያቄ፦ አስፋልቱን ንጣፍ እስካልነካ ድረስ፣ መኪናዬን መንገዱ አጠገብ ማቆም እችላለሁ?**

መልስ፦ የዝቃጭ ማሸጊያ ማንጠፍጠፍ በሚደረግበት ቀን የመንገድ ላይ መኪና ማቆም እና መንዳት በተመረጡ ብሎኮች ላይ (በተያያዘው ካርታ ላይ በቀይ ምልክት የተደረገባቸው) አይፈቀድም፣ እና በዚህ ጊዜ ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ከመንገድ/ አስፋልቱ ንጣፍ ላይ ርቀው መቆየት አለባቸው። የእርስዎ ተሽከርካሪ መንገድ አጠገብ ፓርክ ተደርጐ ነገር ግን በመንገድ ላይ ወይም መንገዱ/ አስፋልቱ ንጣፍ ተጠግቶ እስካልሆነ፣ ይህ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል። ለማረጋገጥ ፎቶ ለኛ ሊልኩ ፈልገው ከሆነ በ DOT_SlurrySeal@Seattle.gov መላክ ይችላሉ።

**ጥያቄ፦ የእኔ ተሽከርካሪ በአሁኑ ጊዜ ተሰናክሏል እና ማንቀሳቀስ አልቻልኩም። ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

መልስ፦ ከዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሂደት በፊት የተሰናከለ ተሽከርካሪን ለማንቀሳቀስ እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን በተቻለ ፍጥነት በ DOT_SlurrySeal@Seattle.gov እኛን ያግኙ እና ከእርስዎ ጋር ዝግጅቶችን ለመደራደር እንሞክራለን። አስቀድመው ስምምነት ያልተደረገባቸው መንገድ ላይ የቀሩ ተሽከርካሪዎች ይጐተታሉ።

### የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር) ንጣፍ መርሐ-ግብር

**ጥያቄ፦ ከሥራ በፊት በምን ያህል ቅድሚያ ማሳሰቢያ ይደርሰኛል?**

A፦ የእኛ ቡድን የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር) ንጣፍ ስራ ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ ሶስት ማሳሰቢያዎችን ለእርስዎ ይልካል። በዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር) በሚደረግባቸው ብሎኮች የሚኖር ወይም ንግድ የሚያንቀሳቅስ እያንዳንዱ ሰው ሥራውን በተመለከተ የመጀመሪያ በራሪ ወረቀት አግኝቷል። ይህ ማሳሰቢያ ለእርስዎ ሁለተኛው በፖስታ የተላከ ነው እና በመጨረሻም፣ እንዲሁም ቡድናችን ከ ዝቃጭ ማሸጊያ(ኣስፋልት እና ጠጠር) ትግበራ 72 ሰአታት በፊት ከበር-ወደ-በር እየሄዱ፣ እና ኮንትራክተሮች ደግሞ ከሶስት ቀናት በፊት "ተሽከርካሪ ማቆም የለም" የሚል ይሰጣሉ።

**ጥያቄ፦ እኔ የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር) ንጣፍ ሥራ በሚሠራበት በዚያው ሳምንት ኮንትራክተሮች እንዲመጡ ቀጠሮ አስይዤ አለሁ። ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

መልስ፦ በዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር) ማልበሱ ሂደት ተመሳሳይ የጊዜ ገደብ በእርስዎ ቤት ወይም ንግድ ቤት እንዲሰሩ የታቀዱ የግል ስራ ተቋራጮች/ ኮንትራክተሮች ቀጠሮ ተይዞ ከሆነ፣ እባክዎን እንደገና ሌላ ቀጠሮ እንዲይዙ ወይም በማንጠፊያው ወቅት በጎዳናው መኪና ሳያሽከረክሩ እና በመንገድ ላይ መኪና ማቆም እንዳይችሉ ሆነው ወደ ቤትዎ እንዲገቡ፣ እና ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ ለስድስት ሰዓታት ያህል ወደ ቤትዎ እንዳይደርሱ ያረጋግጡ። በመንገዱ ላይ የአገልግሎት ፍጆታ መቆራረጥ የሚያካትት የግል የግንባታ ስራ ካለዎት፣ እባክዎን የአስፋልት ንጣፍ መቆራረጥ ስራው ዝቃጭ ማሸጊያ ሥራው ከመጀመሩ በፊት ተሠርቶ እንዲጠናቀቅ እና በቋሚነት እንደገና ወደነበረበት እንዲመለስ ያድርጉ።

Seattle Department of Transportation

**ጥያቄ፡- የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበስ) ሥራ በሚሠራበት በዚያው ቀን እኔ አስፈላጊ የሆነ ቀጠሮ/ የምቀበለው ዕቃ አለኝ። ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

መልስ፡- እርስዎ የሚቀበሉት ዕቃ ቀጠሮ ከዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር) ሂደት ጋር በተመሳሳይ የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት ከሆነ፣ እባክዎን ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ያስይዙ ወይም ዕቃውን የሚያደርስ በእግረኛው መንገድ በኩል እቃዎን መጣል መቻሉን ያረጋግጡ። እርስዎ ያለዎት ቀጠሮ ከዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሂደት ጋር በተመሳሳይ የጊዜ ሰሌዳ የተያዘለት ከሆነ፣ እባክዎን እንደገና ሌላ ቀጠሮ ያስይዙ ወይም እርስዎ በእግረኛ መዳረሻ ብቻ ከእርስዎ መንገድ መውጣት እንደሚችሉ ያረጋግጡ።

## የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሂደት እና ጊዜ አያያዝ

**ጥያቄ፡- የትኞዎቹ መንገዶች ናቸው የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበስ) ጥገና የሚያገኙት?**

መልስ፡- የዝቃጭ ማሸጊያ ጥገና (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበስ) የሚያገኙ መንገዶች በተያያዘው ካርታ ላይ በቀይ ምልክት የተደረገባቸው ብቻ ናቸው። የሆነውም ሆኖ፣ የመደበኛ ትራፊክ ስርዓተ-ጥለታቸው ተጽዕኖ ሊደርስበት ስለሚችል እኛ ቢጫ ምልክት በተደረገበት አካባቢ ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች በሙሉ ማሳሰቢያ እየሰጠን ነው።

**ጥያቄ፡- እኔ የሠራተኞቹ ቡድን በኔ መንገድ ላይ መቼ ሥራ እንደሚጀምሩ እንዴት አውቃለሁ?**

መልስ፡- ከማንኛውም ስራ ቀደም ብሎ እስከ ሶስት ቀናት፣ ተጽዕኖ በሚደርስበት መንገድ ላይ "No Park" ተሽከርካሪ ማቆም የለም የሚል ምልክት ያያሉ። የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሥራ በሚጀምርበት ቀን ጠዋት፣ እርስዎ የሠራተኞች ቡድን በግምት ከንጋቱ 6:30 ሰዓት ላይ ለሥራ ሂደቱ ዝግጅት ሲደርሱ፣ ማናቸውንም ያልተጠበቁ ሁኔታዎችን ሲከልሉ ያያሉ።

**ጥያቄ፡- ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው የዝቃጭ ማሸጊያው (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሂደት ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

መልስ፡- በመደበኛው የዝቃጭ ማሸጊያ (ኣስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሂደት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በግምት አንድ ሰዓት ያህል ይወስዳል። ከሁሉ ይልቅ ጥሩውን ውጤት እንዲሰጥ ከተጠናቀቀ በኋላ መንገዱ እስከ ስድስት ሰዓታት ያህል ድረስ ይዘጋል።

## የህዝብ አገልግሎቶች

**ጥያቄ፡- የዝቃጭ ማሸጊያ (አስፋልት እና ጠጠር ማልበሱ) ሥራ ከኔ የቆሻሻ/ እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ መሰብሰቢያ ቀን አንድ ዓይነት ነው። ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ፧**

መልስ፡- እርስዎ ያሉበት መንገድ በቆሻሻ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ በሚውሉ ማንሻ ቀን ዝቃጭ ሊደረግ የታቀደ ከሆነ የዝቃጭ ማሸጊያው ስራ ከመጀመሩ በፊት ማጠራቀሚያዎቹን ጥዋት በማለዳ ለማንሳት ኣስቀድሞ ባለው ሌሊት መውጣታቸውን እንዲያረጋግጡ ማሳሰቢያ ይደርሰዎታል። የቆሻሻ እና እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የማንሻ ጥያቄዎች፣ ወይም የእርስዎ ቆሻሻ ተነስቶ ካልሆነ እና መነሳት ከነበረበት፣ ጥያቄዎቹ ወደሚከተለው ሊመሩ ይችላሉ፡- DOT_SlurrySeal@seattle.gov።

**ጥያቄ፡- የልጄ የትምህርት ቤት አውቶብስ የዝቃጭ ማሸጊያ ሊሠራ በተባለበት መንገድ ላይ ይቆማል። ይህንን እንዴት ትፈቱታላችሁ?**

መልስ፡- በተለምዶ፣ የትምህርት ቤት አውቶቡስ አገልግሎት ከጠዋቱ 8:45 ሰዓት ላይ ያበቃል እና እንደገና ከሰዓት በኋላ በ2:45 ይቀጥላል። ቡድናችን በዚያ መንገድ ላይ ያለውን የስራ መርሃ ግብር ከጠዋቱ 9:00 ሰዓት እስከ ከሰዓት በኋላ 2:30 ባለው ጊዜ ውስጥ ያስተካክላል።

## ለዝቃጭ ማሸጊያ ጥገና የተመረጡ መንገዶች

**ጥያቄ፡- መንገዶች ለዝቃጭ ማሸጊያ ሥራ እንዴት እንደሚመረጡ?**

መልስ፡- አብዛኛዎቹ የአፈር ወይም ጠጠር የነበራቸውን የቦታዎች/ መንገዶች፣ የሲያትል ከተማ በ1950 ዎቹ እና 1960ዎቹ ውስጥ በርካታ የኪንግ ካውንቲ ክፍሎችን ወደራሷ ጨምራለች። እነዚህ መንገዶች በትንሹ/ በስስ መጠን አስፋልት ተነጠፉ እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሲያትል የመጓጓዣ መምሪያ (SDOT) የአስፋልት ንጣፉን እድሜ ለማራዘም በየጊዜው እንደገና ያሸጋቸዋል። ለዘንድሮው የዝቃጭ ማሸጊያ ጥገና የተመረጠ እያንዳንዱ መንገድ አሁን ባለው የአስፋልት ንጣፍ ዕድሜ እና እንዲሁም በ SDOT ሰራተኞች በቦታው ላይ ተገኝተው በተደረገ ፍተሻ ላይ የተመሰረተ ነው።

**ጥያቄ፡- እኔ የምኖረው በአቅራቢያው ነው፣ ነገር ግን መንገዴ የዝቃጭ ማሸጊያ ጥገና የሚደርሳቸው መንገዶች ዝርዝር ውስጥ አልተካተተም። ወደፊት መንገዴ የዝቃጭ ማሸጊያ ጥገና እንዲደርሰው የምፈልግ ከሆነ ማንን አነጋግራለሁ/ አገኛለሁ?**

መልስ፡- እርስዎ መንገድዎ ለወደፊት ለዝቃጭ ማሸጊያ ጥገና ተጨማሪ ትኩረት ሊሰጠው/ ሊያገኝ ይገባዋል ብለው ካሰቡ፣ እባክዎን የሲያትል የመጓጓዣ ግንኙነት መምሪያ ጉዳዮችን በኢሜይል ለማግኘት ነፃነት ይሰማዎ። እባክዎን DOT_SlurrySeal@seattle.gov ወይም ስልክ 206-775-8742 እኛን ያግኙን።

**ጥያቄ፡- የዝቃጭ ማሸጊያ መርሐ-ግብሩ ሊቀየር ይችላል? ከሆነስ፣ መቼ ነው ማሳሰቢያ የሚሰጠን?**

መልስ፡-መርሐ-ግብር የተያዘለት የዝቃጭ ማሸጊያ ሊለወጥ ይችላል እና ስለ የጊዜ ሰሌዳ ለውጦች መረጃ እያገኙ ለመቆየት ከሁሉ ይልቅ ምርጥ መንገድ በፕሮጀክታችን ኢሜይል አገልግሎት መመዝገብ ነው። የእኛን ድህረ ገጽ ለመጎብኘት እና እራስዎን ወደ ፕሮጀክታችን ኢሜይል ዝርዝር ለመጨመር ከታች ያለውን የQR ኮድ ይቃኙ።